Amharic
Guide to Prostate Cancer

ሕብረተሰባችን ስለ

# ፕሮስቴት ካንሰር

ምን ማወቅ አለበት?



የሕብረተሰባችንን ጤንነት ለማሻሻል በሕብረት መጣር ይገባናል

Cross Cultural Health
crossculturalhealth.org



# ስለ ፕሮስቴት ካንሰር ምን እናውቃለን?

1. ፕሮስቴት ካንሰር በወንዶች ላይ ከሚደርሱ የካንሰር አይነቶች በብዛት የሚደርስ የካንሰር አይነት ነው። ከአምስት ወንዶች አን ዱበዚህ ካንሰር ይለከፋል።
2. በአመት ከ41,000 ወንዶች በላይ በዚህ ካንሰር ምክንያት በአሜሪካን ይሞታሉ። ፕሮስቴት ካንሰርን የማግኛና የማከሚያ የ ተለያዩና የተሻሻሉ ዘዴዎች በመኖራቸው በካንሰሩ የተለከፉ ወንዶችን ሕይወት ለማራዘምና ጤናቸውን ለማሻሻል ተችሎዋል።
3. ፕሮስቴት ካንሰር በግዜው ከተገኘ ለበሽታው የሚደረጉ ሕክምናዎች በይበልጥ የመሥራት እድል አላቸው።

# ፕሮስቴት ካንሰር ምንድን ነው?

የፕሮስቴት ዕጢ የወንዶችን የዘር ፍሬ የሚያመላልሰውን ፈሳሽ
የሚሰራ የወሲብ ዕጢ ነው።

<u>የፕሮስረቴት ዕጢ የት ይገኛል?</u>

የፕሮስቴት ዕጢ ከአንጀታችን ፊት ለፊት የሚገኝ ሲሆን፤ ሽንትን ከሽንት ከረጢት ወደ ውጭ የሚወስደ ሚገኝ ዕጢ ነው።




ስዕል1

# ለዚህ ካንሰር የተጋለጠ ማን ነው?

**ማንኛውም ወንድ ልጅ በፕሮስቴት ካንሰር የመያዝ እድል አለው**

### ለዚህ ካንሰር በበለጠ የምትጋለጡት

- የቤተሰብ መሰረታችሁ ከአፍሪካ ከሆነ
- ዕድሜአችሁ ከ65 ዓመት በላይ ከሆነ
- ቅባት የበዛበት ምግብ የምትመገቡ ከሆነ
- በብየዳና በኤሌክትሮፕሌቲንግ ሥራ ለረዥም ጊዜ የሠራችሁ ወይንም ካድሚየም ለሚባል የብረት አይነት ሰውነታችሁ ተጋልጦ ከሆነ
- በቤተሰባችሁ ታሪክ ውስጥ በፕሮስቴት ካንሰር ከዚህ በፊት ተይዞ የነበረ የቤተሰብ አባል ካለ።

በዚህ በሽታ የሚለከፉ ወንዶች በተለያዩ ጥናቶች በተገኙ አመልካች ምክንያቶች የተጋለጡ ብቻ አይደሉም። ማንኛውም ወንድ ልጅ ወንድ በመሆኑ ብቻ በፕሮስቴት ካንሰር የመያዝ እድል እንዳለው እንረዳ።

# በፕሮስቴት ካንሰር የመለከፍ ቅድመ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ፕሮስቴት ካንሰር አብዛኛውን ጊዜ ቅድመ ምልክቶች የሉትም። ነገር ግን ከዚህ በታች የተጠቀሱት ችግሮች ካጋጠሙዋችሁ ባስቸኳይ ወደ ሐኪም ቤት ወይንም ክሊኒክ ሂዱ።

- ሽንታችሁን በምትሸኑበት ወቅት በዝግታ የመፍሰስ ወይንም ቁርጥ ቁርጥ እያለ የመፍሰስ ችግር ካለባችሁ።
- ሽንት መሽናት የመጀመር ወይንም የመጨረስ ችግር ካለባችሁ።
- ቶሎ ቶሎ በቀን ከሚገባችሁ በላይ የመሽናት ችግር ካለባችሁ። በተለይም በምሽት ጊዜ ከሆነ።
- በምትሸኑበት ወቅት በሽንታችሁ ውስጥ ደም ካያችሁ።
- በምትሸኑበት ወቅት የማቃጠል ወይንም የማመም ስሜት ከተሰማችሁ።
- በዝቅተኛው የጀርባችሁ ክፍል ወይንም በላይኛው የጭናችሁ ክፍልና አካባቢ ህመም የሚሰማችሁ ከሆነ።

**ማስተሰወሻ፤-** ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከል አንዱ አንኳን ከተሰማችሁ ወደ ክሊኒክ ወይንም ሐኪም ቤት ለምርመራ መሄድ አትርሱ

## ፕሮስቴት ካንሰርን እንዴት ማግኘት ይቻላል

ሐኪማችሁ ፊንጢጣችሁን በጣቶቹ በመዳሰስ ፕሮስቴት ካንሰር ካለባችሁ ማወቅ ይችላል። ይህ የፊንጢጣ ምርመራ በመባል ይታወቃል። በተጨማሪም ሐኪማችሁ የደም ምርመራ በማዘዝ በደማችሁ ውስጥ የፕሮስቴት ካንሰር ምልክቶች እንደሉ በመመርመር ማወቅ ይችላል። ይህ ፕ.ስ.አ. (ፕሮስቴት ስፔስፊክ አንቴጅን) የደም ምርመራ ይባላል።

## ሐኪም ቤት መቼ ለፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ መሄድ አለብን?

ማንኛውም ወንድ ልጅ ዕድሜው ከ50 ዓመት በላይ ከሆነ ሐኪም ቤት ወይንም ክሊኒክ በዓመት አንድ ጊዜ በመሄድ የፊንጢጣ ፍተሻና የፕ.ስ.አ. የደም ምርመራ ማድረግ አለበት።

ወጣት ወንወዶች ለበሽታው የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ከሆነ ስለ ፕሮስቴት ካንሰር ከሐኪም ጋር መነጋገር ይኖርባቸዋል።

## ሐኪም ፕሮስቴት ካንሰር ሊኖርባችሁ ይችላል ብሎ ካለ ምን ማድረግ አለበት?

ሐኪም በፍተሻም ሆነ በደም ምርመራ ወቅት የፕሮስቴት ካንሰር ምልክቶች አሉ ብሎ ካመነ ተጨማሪ ፍተሻዎችና ምርመራዎቸን ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪ ሊያአደርጋቸው ከሚችላቸው ምርመራዎች መካከል ኤክስሬ፤ አልትራ ሳውንድና የደም ምርመራ ሲሆኑ እንዲሁም ሐኪማችሁ ባዮፕሲ በሚባል የሕክምና ዘዴ ከፕሮስቴት ዕጢአችሁ ላይ ቁራጭ አካል በመውሰድ በማጉያ መነፅር ስር መመርመርም ይችላል።

**ማስታወሻ፤- ፕሮስቴት ካንሰር ሊኖርባችሁም ላይኖርባችሁም ስለሚችል ። ሐኪም ተጨማሪ ምርመራዎችን ለማድረግ በቀጠራችሁ ጊዜ ሐኪም ቤት መሄድን አትርሱ። <u>ቁርጡን ማወቅ ለሕይወት ይበጃልና</u>።**

## በተደረጉት ምርመራዎች ውጤት ፕሮስቴት ካንሰር እንዳለብን ካረጋገጥን ምን ማድረግ አለብን?

የምርመራዎቹ ውጤት ፕሮስቴት ካንሰር እንዳለብን ካረጋገጠ ሐኪም የትኛው የሕክምና ዘዴ ወደ ጤንነት እንደሚመልሰን ይነረናል። ፕሮስቴት ካንሰርን የማከሚያ ዘዴዎች ቀዶ ጥገና እንዲሁም የተለያዩ መድሃኒቶችን (ኪሞ ቴራፒን) ያጠቃልላሉ። ሐኪሙና እናንተ በመነጋገር ለእናንተ የሚበጃችሁን መንገድ መወሰን ይኖርባችኋል።

**ማስታወሻ፤- ፕሮስቴት ካንሰርን በተሳካ ሁኔታ ለ መከላከል የሚቻለው በጊዜው ከተደረሰበት መሆኑን አትርሱ። በመጀመር ላይ ያለ ፕሮስቴት ካንሰር አመልካች ልዩ ምልክቶች <u>የሉትም</u>። ፕሮስቴት ካንሰርን በቅድሚያ ማግኘት የሚቻለው በየጊዜው ተራ የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ በማድረግ ብቻ ነው።**

ለቤተሰባችሁ፤ ለጓደኞቻችሁና ለሕብረተሰባችሁ ሸክም ከመሆን እንድትድኑ የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ በየጊዜው ማድረግን አትዘንጉ።

# መዝገበ ቃላት

ባዮፕሲ፤- የቀዶ ጥገና በመጠቀም ቁራጭ አካል ከሰውነት ክፍላችን በመውሰድ በአጉይ መነፅር በመጠቀም ካንሰር እንዳለናእንደሌለ የመመርመሪያ ዘዴ ነው። ባዮፕሲ ከሁሉምየካንሰር መመርመሪያ ዘዴዎች ዋንኛው ነው።

ፊኛ (ብላደር)፤- በቆዳ የተሠራ ሽንታችን በሽንት ቱቦ(ዩሬትራ) በኩል እስኪወገድ ድረስ የሚጠራቀምበት ከረጢት ነው(ስእል 2 ተመልከቱ)

ካድሚየም፤- ነጭ ሰማያዊ መልክ ያለው የተሊያዩ የብረት አይነቶችን ለማጠንከር የሚጠቅም የብረት ዘር ነው።

ኪሞ ቴራፒ፤- እንደ ካንሰር ያሉ በሽታዎችን መድሀኒቾችን በመጠቀም የመከላከያ ዘዴ።

ዕጢ(ግላንድ)፤- የተለያዩ የሰውነት ፈሳሾችን የሚሠራና ለሰውነታችንየሚጠቅሙትን ወደ ደማችን እንዲቀላቀሉ ሲያደርግ የማይጠቅሙትን እንዲወገዱ የሚረዳ የሰውነት ክፍል ነው ።

ፕሮስቴት፤- ከወንዶች ፊኛ ስር የሚገኝ ዕጢ(ስዕል2ን ተመልከቱ)

የወንድ ዘር(ስፐርም)፤- በወንድ የወሲብ የሰውነት ክፍል የሚመረት ሲመን በሚባል ፈሳሽ ውስጥ የሚዋኝና ከሴቱዋ እንቅላል ጋር በመዋሃድ

አዲስ ሕይወት ሲፈጥር የሚችል ሴል ነው።

የፊንጢጣ(ሬክታል) ምርመራ፦ ሐኪሞች በፊንጢጣ በኩል በጣታቸው ፕሪስቴትን የሚመረምሩበት ዘዴ ነው(ስእል 2 ተመልከቱ) ዲጂታል በሚል ስምም ይታወቃል።

አልትራ ሳውንድ፦ ከፍተኛ ሞገድ ያለው ድምፅ በመጠቀም በሰውነታችን የውስጥ ክፍል ካንሰር ካለ የመፈለጊያ ዘዴ ነው። አልትራሶኖግራፍ በሚል ስምም ጭምር ይታወቃል።




ስእል ቀ.2

